# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የአርብ ፕሮግራም

**የአርብ ፕሮግራም የምጸልይበት፣ የምንነቃቃበትና የምንማርበት ፕሮግራም ነው። የምንችል ሁሉ እንድንካፈል እናበረታታለን። ጌታ ይባርካችሁ!**

ስለ አራቱ መንፈሳዊ ሕጎች ሰምተዋል?

1) እግዚአብሔር ስለሚያፈቅረን ለሕወታችን አስደናቂ እቅድ ሰጥቶናል።

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" ዮሐንስ 3፡16

2) ሰው ኃጢአተኛ የሆነ ባህርይ ስላለውና በዚህም ምክንያት ከእግዚአብሔር ስለ ተለየ እግዚአብሔር ለእርሱ ያለውን ፍቅርና እቅድ ሊለማመድ አይችልም።

"ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል።" ሮሜ 3፡23

3) ኢየሱስ ክርስቶስ ለኛ በመሞቱ በእርሱ በኩል ብቻ ሰው ወደ እግዚአብሔር ይደርሳል።

"እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" ዮሐንስ 14፡6

4) ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛችንና ጌታችን አድርገን በመቀበል እግዚአብሔር አምላክ ለኛ ያለውን ፍቅርና እቅድ ልናውቅና ልንለማመድ እንችላለን።

"ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።" ዮሐንስ 1፡12

*"በሚመጣው ዘመን ያዕቆብ ሥር ይሰድዳል፥ እስራኤልም ያብባል ይጨበጭብማል፤ በፍሬያቸውም የዓለሙን ፊት ይሞላሉ።" (ኢሳ. 27፡6)*



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-
773-886-0818 (ሲሳይ)
773-865-6102 (ብረሃኑ)
773-507-0194 (ጋሽ አያሌው)
773-910-0485 (ፒተር)
773-961-5332 (ጌቱ)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10



**በችካጎና አካባቢው ለምትገኙ አብያተክርስቲያናት በሙሉ**

**ታላቅ የመነቃቂያና የአገልጋዮች ስልጠና በቺካጎ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን**

**ቀን፡** ቅዳሜ July 29, 2017 — **አገልጋይ፡** ፓስተር ዶር ቤዛለም

**ርዕስ፡** መጽህፍ ቅዱሳዊ አመራር — **ቦታ፡** በቺካግ የምስራች ቤተ ክርስቲያን

በተጨማሪም አርብ (July 28) ከ7p.m. ጀምሮ እሁድ (July 30) ከ1፡30p.m. ጀምሮ ባለው የቤተክርስቲያኒቱ መደበኛ ፕሮግራም ላይ ያገለግላል።

**ኑ የእግዚያብሄርን ህዝብ ወደታየለት የህይወት ከፍታ እናድርስ!**

"ሁላችን የእግዚያብሄርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት ሙሉ ሰውም ወደ መሆን የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመስራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።" (ኤፌ. 4፡12)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**July 16, 2017** | **ሐምሌ 9፤ 2009 ዓ.ም.**

## የእለቱ ፕሮግራም መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | ወንድም ረድኤቱ ካሳ |
| አምልኮ...................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም  አያሌው አስፋው |
| ቃል ........................... | እሕት ሰናይት ከበደ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

"በእርሱም ከጠላቶቻችን እጅ ድነን
በዘመናችን ሁሉ ያለ ፍርሃት በቅድስናና
በጽድቅ በፊቱ እንድናገለግለው
ሰጠን።" (ሉቃ. 1፡74-75)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም ከከቤ አስረስ | ቅዳሜ | 4701 B S. Woodlawn, Chicago, IL 60615 |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 6602 N. Damen Ave., Chicago IL 60626 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ማክሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ  ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ዴሌቦ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ያለንን እንስጥ!

ብዙ ቅዱሳን ለምን አታገለግሉም ሲባሉ "እኔማ ለማገልገል ብቁ አይደለሁም፤ ፕሮግራም ከተካፈልኩ መች አነሰኝ ... ወዘተ" በማለት ሲመልሱ ይደመጣል። መጽሐፍ ቅዱሳችንን ሲንመረምር ግን የምናገኘው እውነት እግዚአብሔር የጠራቸውን ብቁ ያደርጋል እንጂ ብቁዎችን ፈልጎ አይጠራም። ለዚህ ብዙ ማስረጃ መጥቀስ እንችላለን። ሙሴ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብጽ እንዲያወጣ ሲጠራው አገልግሎቱን ላለመቀበል ከግዚአብሔር ጋር ብዙ ክርክር ገጥሞ ነበር። ቃሉ "ሙሴም እግዚአብሔርን፡- ወደ ፈርዖን የምሄድ የእስራኤልንም ልጆች ከግብፅ የማወጣ እኔ ማን ነኝ? አለው" ይለናል (ዘጸ 3፡11) በመቀጠልም ሙሴ ጥሪውን ላለመቀበል "ጌታ ሆይ፥ እኔ አፌ ኰልታፋ ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ" በማለት ለእግዚአብሔር ሲመልስ እናነባለን። (ዘጸ 4፡10) ሙሴ ያነሳ የነበረው እኔ ብቁ አይደለሁም የሚል ጥያቄ ነበር። እግዚአብሔር ግን በታምራትና በቃል አንተ በራስህ ብቁ አይደለህም እኔ ግን ብቁ ነኝ ይለው ነበር። እግዚአብሔርም አለው "የሰውን አፍ የፈጠረ ማን ነው? ዲዳስ ደንቆሮስ የሚያይስ ዕውርስ ያደረገ ማን ነው? እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን? እንግዲህ አሁን ሂድ፥ እኔም ከአፍህ ጋር እሆናለሁ፥ የምትናገረውንም አስተምርሃለሁ አለው።" (ቁ. 11-12)

ወገኖቼ! እርግጥ ነው እግዚአብሔር ለመረጣቸው ብቃትን ይሰጣል እንጂ ብቁዎችን እየመረጠ አይጠራም። አለምን የገለባበጡ ሐዋሪያት የትምሕርት ብቃትና የኃብት ብዛት ወይንም ባለስልጣናት የነበሩ አልነበረም። ተራ ሰዎች (አብዛኞቹ ዓሳ አጥማጆች ነበሩ)። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ብቃትን ከሰጣቸው በኋላ በታላቅ ኃይልና መገለጥ የወንጌሉን እሳት አቀጣጠሉ። እግዚአብሔር በዘመናት መካከል የጠራቸውን ሰዎች እያስታጠቀ ሃሳቡን እንዲያገለግሉ ብቃትን ሰጥቷቸዋል። ስለዚሕም ሐዋሪያው ጳውሎስ ሲመሰክር "ለአገልግሎቱ ሾሞኝ ታማኝ አድርጎ ስለ ቈጠረኝ፥ ኃይል የሰጠኝን ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታችንን አመሰግናለሁ" ይላል። (1ጢሞ 1፡12) ሐዋሪያው አገልግሎት ሹመት እንደሆነ ይነግረናል። ለዚህ ሹመት ደግም የምንበቃው እግዚአብሔር ታማኝ አድርጎ ስለቆጠረን ነው። እኛ ታማኝ ሆነን ወይንም ብቃት ኖሮን ሳይሆን እርሱ "ነህ"፤ "ነሽ" ስላለን ብቻ ነው። ለዚህ ሹመት የሚሆነውን ኃይልም የሚሰጠን እርሱው ነው። እንግዲህ ሐዋሪያው እንዳለ "ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነው።" (ሮሜ 11፡36)

ወገኖቼ! የኛ ድርሻ እራሳችንን ለርሱ ማቅረብ ነው። ብቃትንና ኃይልን ግን የሚሰጥ እርሱ ነው። እርሱ በእጃችን ያሉትን ሁለት አሳና አምስት እንጀራ ከሰጠነው ታምራትን መስራት የርሱ ፋንታ ነው። ዛሬ የት ጋር ነው እግዚአብሔር እንድንቆም የሚጠይቀን? ምንድነው በእጃችን ያለው? ያለንን ትንሹን ነገር (እራሳችንን) ለእርሱ ብናቀርብ እርሱ ታምራትን ያደርጋል። እግዚአብሔር በሰጠን መክሊት መጠን እንጂ ባልሰጠን መክሊት መጠን አይጠይቀንም። አንድ መክሊት ካለን የአምስት መኪሊት ስራ አይጠብቅብንም። ነገር ግን ባለን (በተሰጠን) ልክ ለጌታ ስራ እንቁም!